## ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ መሰናበት ፡ በወንጀለኛና ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያለው ፡ አቀዋም ።

ከሳሽ ፡- ጌታቸው ፡ ብርሃኔ ፤
ተከሳሽ ፡- የኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ባንክ ፡ (አክሲዮን ፡ ማኅበር) ፡[1]

ከዳንኤል ፡ ኃይሌ ፡ *

ከሳሽ ፡ በመልስ ፡ ሰጭ ፡ ባንክ ፡ ተቀጥሮ ፡ ሲሰራ ፡ እሱና ፡ ሌሎች ፡ የባንኩ ፡ ሠራተኞች ፡ የ፲፪ሺ ፡ ብር ፡ ቼክ ፡ መንዝረው ፡ (ወስደዋል) ፡ አጥፍተዋል ፡ በመባል ፡ ከሥራ ፡ በጥቅምት ፡ ፳፰ ፲፱፻፸፩ ፡ ዓ. ም. (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) ተሰናበተ ። በተጨማሪም ፡ ዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ንና ፡ ፮፻፶፮(ሀ)ን ፡ ተላልፈ ዋል ፡ በማለት ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ አቀረበባቸው ።[2] የወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ከተመሠረተ ፡ ከሀያ ፡ ዘጠኝ ፡ (፳፱)ወር ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ የዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ማስረጃ ፡ የአሁኑን ፡ ከሳሽ ፡ ጥፋተኛ ፡ ስለማያደርገው ፡ ክሱ ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ፩፻፵፩ ፡ መሠረት ፡ እንዲሠረዝና ፡ የአሁን ፡ ከሳሽ ፡ በነፃ ፡ እንዲለቀቅ ፡ አዘዘ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሳሽ ፡ ከሥራው ፡ ተሰናብቶ ፡ ያልሠራበት ፡ ጊዜ ፡ ደመወዝ ፤ የዓመት ፡ ፈቃድም ፡ ጭምር ፡ እንዲከፈለው ፤ የሞራል ፡ ካሣና ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ የወ ጣው ፡ ገንዘብ ፡ በጠቅላላው ፡ በኪሣራ ፡ መልክ ፡ ፲፩ሺ፱፻፳፰ ፡ ብር ፡ ከ፱ ፡ ሣንቲም ፡ እንዲከፈለው ፡ በማለት ፡ ይህን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ አቀረበ ። በተጨማሪም ፡ ተከሳሽ ፡ ከሳሽን ፡ በድሮው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲመልሰውና ፡ ክሱ ፡ ያደረሰውን ፡ የስም ፡ ማጉደፍ ፡ ውጤት ፡ ለመሻር ፡ ተከሳሽ ፡ የስም ፡ ማደሻ ፡ ማስታወቂያ ፡ እንዲገልጽና ፡ እንዲጽፍ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥለት ፡ ጠይቋል ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ ከሳሽ ፡ ከሥራው ፡ የተሰናበተው ፡ ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ፩ሺ፩፻፶፱ ፡ በኪሣራ ፡ መልክ ፡ እንዲከፈለው ፡ አዘዘ ። ከሳሽ ፡ በሥራው ፡ ላይ ፡ እንዲመለስ ፡ ያቀ ረበውን ፡ አቤቱታ ፡ ግን ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሳይቀበለው ፡ ቀርቷል ።

ይህ ፡ ፍርድ ፡ ሁለት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ጥያቄዎችን ፡ እንድንጠይቅ ፡ ያደርገናል ፤

፩/ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ክስ ፡ ከመሰማቱ ፡ በፊት ፡ እንደ አሁን ፡ ተከሳሽ ፡ ያሉትን ፡ ንጹሕ ፡ ሰዎች ፡ መብት ፡ ጠብቆ ፡ ክስ ፡ እንዳይቀ ርብባቸው ፡ ለማድረግ ፡ በቂ ፡ መፍትሔ ፡ (ማገጃ) ፡ አሉትን ?

---

* ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ ቀ ፡ ኃ ፡ ሥ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፤ አ/አበባ ። ደራሲው ፡ ጽሑፉን ፡ ሲያዘጋጅ ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ምክር ፡ ለሰጡቸው ፡ ፕሮፌሰር ፡ ስክላርን ፡ ያመሰግናል ።

1. ከሳሽ ፤ ጌታቸው ፡ ብርሃኔ ፤ ተከሳሽ ፡ የኢ.ን.ባንክ ፡ (አክ.ማ.) ፡ ከ.ፍ/ቤት ፤ አ.አ. ፡ ፲፱፻፶፬ ፡ የፍ.ብሔር ፡ መዝገብ ፡ ቁ. ፩ሺ፮፻፶፬/፶፬ ፡ (ያልታተመ) ።

2. ከሳሽ ፤ ዓቃቤ ፡ ሕግ ፤ ተከሳሽ ፤ ሥዩም ፡ ደጀኔና ፡ ግብረ ፡ አበሮቹ ፡ (ከ.ፍ/ቤት ፤ አ.አ. የወንጀል ፡ መዝገብ ፡ ቁ. ፩ሺ፩፻፲፪/፸፯ ፡ (ያልታተመ) ። አንቀጽ ፡ ፮፻፶፮ ፡ ስለ ፡ አታላይነት ፡ ሲናገር ፡ አንቀጽ ፡ ፴፯ ፡ ስለ ፡ አባሪነት ፡ ይናገራል ።

፪/ የአገሪቷስ ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ሕጎች ፡ ካለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ቸው ፡ የሚሰናበቱትን ፡ የተበደሉ ፡ ሠራተኞች ፡ መብት ፡ በደንብ ፡ ይጠብቃ ሉን ?

፫/ በወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመሰማቱ ፡ በፊት ፡ ስለሚደረገው ፡ የክስ ፡ ማጣራት ፡ ዘዴ ።

"የማንኛውም ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የአሠራሩ ፡ ቅልጥፍናና፡ ጥቅሙ ፡ የሚለካው ፡ በተመጣጣኝ ፡ መንገድ ፡ ለሕብረ ፡ ሰብ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆኑ ፡ ሁለት ፡ ግቦች ፡ መሠረት ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ በተፋጠነና ፡ ሕጋዊ ፡ በሆነ ፡ መንገድ ፡ ጥፋተኞቹን ፡ በማቅረብ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማድረግ ፡ የሚችልበትንና ፡ ንጹሕ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሳይነኩ ፡ ሊታለፉ ፡ የሚቻልበትን ፡ ሁኔታ ፡ ለማቅረብ ፡ መቻሉ ፡ ነው" ።[3] የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መሠረታዊ ፡ ዓላማው ፡ እነዚህን ፡ ሁለት ፡ ተቃራኒ ፡ መስል ፡ ተግባሮች ፡ ማዋሀድ ፡ (ማስታረቅ) ፡ ነው ። የአሁኑ ፡ ክሳሽ ፡ ክሱ ፡ ከተመሠረተ ፡ ከ፳፱ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ በነፃ ፡ መለቀቁን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ የሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ ሕግ ፡ ፪ኛው ፡ ግብ ፡ ይሆናል ፤ ይኸውም ፡ ንጹሕ ፡ ሰዎች ፡ ሳይነኩ ፡ የሚ ታለፉበት ፡ መንገድ ፡ ነው ።

ዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ በተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ የማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።[4] ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የማይችለው ፡ ተከሳሹን ፡ ጥፋተኛ ፡ ለማድረግ ፡ በቂ ፡ የሆነ ፡ መረጃ ፡ የሌለ ፡ መሆኑን ፡ የተረዳው ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ።[5] በመሠረቱ ፡ ለዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ እንዲያውም ፡ የምርመራ ፡ መዝገብ ፡ ለሚያዘጋጁት ፡ ፖሊሶች ፡ ማን ፡ ሊከሰስ ፡ እንደሚ ችልና ፡ እንደማይችል ፡ የመወሰኛ ፡ አንስተኛ ፡ የሆነ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲሰጡ ፡ ቢደረግ ፡ አን ቃወምም ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ዓይነት ፡ ሥልጣን ፡ ከሰጠን ፡ ከሥልጣን ፡ አላፊ ፡ ተግባሮች ፡ እንዳይሠሩ ፡ የሚደረግበትን ፡ ዘዴ ፡ መፈለግ ፡ አለብን ። በኛ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ የዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አስተሳሰብ ፡ ወይም ፡ መረዳት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለመክሰስ ፡ ወይም ፡ ላለመክሰስ ፡ ለሚደረገው ፡ ውሳኔ ፡ የሚያስፈልገው ። ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ለመክሰስ ፡ ከወሰነ ፡ ለከባድ ፡ የግድያ ፡ አገዳደል ፡ ወይም ፡ ከባድ ፡ ለሆነ ፡ የወንበዴነት ፡ ሥራ ፡[6] ካልሆነ ፡ በቀር ፡ ተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ወዲያው ፡ ክስ ፡ ለማ ቅረብና ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ ለማቅረብ ፡ ውሳኔው ፡ የመጨረሻ ፡ ነው ። በላይ ፡ በተ ጠቀሱትም ፡ ሁኔታዎች ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ የቀዳሚው ፡ ምርመራ ፡ ወይም ፡ ነገሩ ፡ የሚ ሰማበት ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ተከሳሹን ፡ በነፃ ፡ ለመልቀቅ ፡ ስለማይችሉ ፡[7] የዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ አስተሳሰብ ፡ ተከሳሹ ፡ ላይ ፡ ክሱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ እንዲቀርብበት ፡ ለማድረግ ፡ በቂ ፡ ነው ። ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በጭካኔ ፡ መንፈስ ፡ እንኳ ፡ ተነሣሥቶ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ቢያስብ ፡ ጉዳዩ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ተሰምቶ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክሱን ፡ አላ ስረዳም ፡ ብሎ ፡ እስከሠረዘው ፡ ድረስ ፡ ተከሳሹ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ ሌላ ፡ መፍትሔ ፡ የለውም ።[8] ይህም ፡ ዓይነቱ ፡ የፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ውሳኔ ፡ እንደ ፡ ክሱ ፡ ዝግጅት ፡ ፍርድ ፡

3. ስታንሊ. ዚ. ፊሸር ፡ የኢ.ወ.መ. ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ (፲፱፻፷፱) ፡ ገጽ ፡ ፩ ፡ (እንግሊዝኛ) ።
4. አ. ፵ ፡ የወ.መ.ሥ.ሥ. ሕግ ።
5. አ. ፵፪ (1) የወ.መ.ሥ.ሥ. ሕግ ።
6. አ. ፹ ፡ የወ.መ.ሥ.ሥ. ሕግ ።
7. አ. ፺፬ ፡ የወ.መ.ሥ.ሥ. ሕግ ።
8. አ. ፩፻፵፩ ፡ የወ.መ.ሥ.ሥ. ሕግ ።

ቤቱ ፡ ክሱን ፡ መስማት ፡ በጀመረበት ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ሊሆን ፡ ወይም ፡ ላይ ሆን ፡ ይችላል ።

በአሁኑ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ የክሱን ፡ ፋይል ፡ ስንመረምረው ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ተከሳሾች ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ ለመመሥረት ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ የለውም ፡ ነበር ። የዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ መነሻው ፡ ከጀርባው ፡ ላይ ፡ "ለኔ ፡ እንደታወቀኝ" ፡ "ሥዩም" ፡ "፫፻፶፱/፷" የሚሉ ፡ ጽሑፎች ፡ የሚገኙበት ፡ ራሱ ፡ ቼኩ ፡ ነበር ።[9]

ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ባቀረበው ፡ ጥያቄ ፡ መሠረት ፡ በ፲፱፻፳፬ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) የወንጀለኛ ፡ ምርመራ ፡ ክፍል ፡ በተከሳሾች ፡ ላይ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ ምርመራ ፡ አድርጓል ። የምርመራው ፡ ውጤት ፡ ግን ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ከዘጠኝ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ካቀረበው ፡ የክስ ፡ ዝግጅት ፡ ጋር ፡ እንደማስረጃ ፡ ተያይዞ ፡ አልቀረበም ። የእጅ ፡ ጽሕፈት ፡ መርማሪውም ፡ (ኤክስፐርት) ፡ በጥር ፡ ፲፯/፲፱፻፳፯ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) በሰጠው ፡ የምስክርነት ፡ ቃል ፡ የተከሳሾቹ ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍና ፡ ከቼኩ ፡ ጀርባ ፡ ያለው ፡ የእጅ ፡ ጽሑፍ ፡ እንደማይመሳሰል ፡ ገልጿል ። በእጅ ፡ ጽሑፎቹ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ካላስረዳ ፡ ከቅድሚያውኑ ፡ ክሱን ፡ ሊመሠርት ፡ ስለማይችል ፡ ተከሳሾቹ ፡ ክስ ፡ ቀርቦባቸው ፡ መጉላላት ፡ የለባቸውም ፡ ነበር ።

ካለ ፡ አግባብ ፡ የተከሰሰ ፡ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ ክሱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ከተሰማ ፡ በኋላ ፡ እንጂ ፡ ከዛ ፡ በፊት ፡ መብቱ ፡ ሊጠበቅ ፡ አለመቻሉ ፡ ክሱን ፡ በማጣራት ፡ ዘዴ ፡ በኛ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ ጉድለት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ አለመስተካከል ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ አላቀርብም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ ብንመለከተው ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ይታያል ። የዓቃቤ ፡ ሕግ ፡ ክስ ፡ አላቀርብም ፡ ማለት ፡ በክስ ፡ አቤቱታ ፡ ለሚያስቀጣ ፡ ወንጀል ፡ አቤቱታ ፡ አቅራቢው ፡ የግል ፡ ክስ፡ እንዲያቀርብና ፡ በክስ ፡ አቤቱታ ፡ ለማይቀርቡ ፡ ወንጀሎች ፡ የዓቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ውሳኔ ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ በማቅረብ ፡ ለመቃወም ፡ ያስችላል ።[10]

የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕጋችን ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ አላቀርብም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ክሱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ስላለው ፡ ሁኔታ ፡ ጥሩ ፡ መፍትሔ ፡ መስጠቱ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ እስራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ቢረዳም ፡ የእንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ መፍትሔ ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ በወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ያለመኖር ፡ ጥፋተኛ ፡ ያልሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ያላግባብ ፡ እንዲሰቃዩ ፡ ያደርጋል ። የዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ አላቀርብም ፡ ማለት ፡ የክሱን ፡ ማቅረብ ፡ ግዴታ ፡ ከመንግሥት ፡ ወደ ፡ ግል ፡ ከሳሽ ፡ ያዛውረዋል ፡ እንጂ ፡ ክሱን ፡ አይዘጋውም ። ክስ ፡ የማቅረብ ፡ ውሳኔው ፡ ግን ፡ ግለሰቡን ፡ በክስ ፡ ወጥመድ ፡ ከማስገባቱም ፡ በላይ ፡ በሕብረ ፡ ሰቡ ፡ ላይ ፡ ስለተከሰሰው ፡ ሰው ፡ የሚያመጣውን ፡ የአስተሳሰብ ፡ ለውጥ ፡

---

9. ዓቃቤ ፡ ሕጉም ፡ ምስክሮች ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ። የምስክርነት ፡ ቃላቸው ፡ ያስረዳው ፡ ግን ፡ ቼኩ ፡ ባንክ ፡ መድረሱን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

10. አንቀጽ ፡ ፭፻ ፡ ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የማለት ፡ ውጤት ፡ (፩) ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ በማቅረብ ፡ ብቻ ፡ የሚያስቀጣ ፡ የወንጀል ፡ ነገር ፡ በቁጥር ፡ ፭፻ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ (ሀ) ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የማለት ፡ ውሳኔ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ በቁጥር ፡ ፭፻ ፡ ለተጠቀሰው ፡ ተገቢ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የግል ፡ ክስ ፡ እንዲያቀርብ ፡ በጽሑፍ ፡ ይፈቅድለታል ። የዚሁም ፡ ውሳኔ ፡ ግልባጭ ፡ ክሱን ፡ ለማየት ፡ መብት ፡ ላለው ፡ ፍ ፡ ቤት ፡ መላክ ፡ አለበት ፡ (፪) ፡ የክስ ፡ አቤቱታ ፡ ማቅረብ ፡ ሳያስፈልግ ፡ የሚያስቀጣ፡ ወንጀል ፡ በቁጥር ፡ ፭፻ ፡ ንዑስ ፡ ቁጥር ፡ ፩ (ሀ) ፡ መሠረት ፡ ክስ ፡ አይቀርብም ፡ የማለት ፡ ውሳኔ ፡ ዐቃቤ፡ ሕጉ ፡ የሰጠ ፡ እንደሆነ ፡ በቁ. ፭፻ ፡ የተጠቀሰው ፡ ተገቢ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የዐቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ውሳኔ ፡ ከተቀበለበት ፡ ጊዜ ፡ አንስቶ ፡ በሠላሳ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ዐቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስን ፡ እንዲያቀርብ ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ።

ስንመለከት ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕጋችን ፡ አንዱን ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ይዞ ፡ መከተል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ አለመስተካከል ፡ እንዳመጣ ፡ በግልጽ ፡ ያሳየ ናል ።

እርግጥ ፡ ነው ፡ ተከሳሹ ፡ ከቦታ ፡ ቦታ ፡ እንዳይዘዋወር ፡ ከተገደደ ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ሕግ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ቁጥር ፡ ፩፻፸፯—፩፻፹፱ ፡ በተደነገገው ፡ መሠረት ፡ አቤቱታውን፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ። አንቀጽ ፡ ፩፻፸፯ ፡ (፩) ፡ እንደሚያሳየው ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ የተገደደ ፤ እንዳይዘዋወር ፡ የተከለከለ ፤ የተያዘ ፡ ወይም ፡ የታሰረው ፡ ሰው ፡ ሲሆን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ አድራጐት ፡ እንዲወገድለት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱን ፡ ለመ ጠየቅ ፡ የሚችለው ። ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ሁኔታ ፡ ግን ፡ ሁልጊዜ ፡ ላይደርስ ፡ ስለሚችል ፡ የዓቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚወስደውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመቃወም ፡ መስጠት ፡ ስላለበት ፡ መብት ፡ ያሰብነውን ፡ ሀሳብ ፡ አይለውጠውም ።

ክሱ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመሰማቱ ፡ በፊት ፡ ለዚህ ፡ ዓይነቱ ፡ ጉዳይ ፡ መፍትሔ ፡ ያለመኖሩ ፡ ሌላ ፡ መድኅን ፡ እንዳይኖር ፡ አያደርገውም ። ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ ሳይኖርበት ፡ የቀረበ ፡ እንደሆነ ፡ ተበዳዩ ፡ ወገን ፡ በአንቀጽ ፡ ፬፻፲፬ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅ ጫ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ የወንጀል ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ወይም ፡ ከውል ፡ ውጭ ፡ ስለሚ ደርስ ፡ አላፊነት ፡ ሕግ ፡ ባሉት ፡ አንቀጾች ፡ መሠረት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ለማ ለማቅረብ ፡ ይችላል ።[11] በፍርድ ፡ ቤት ፡ የክስ ፡ መሰማት ፡ ሥራ ፡ ሁልጊዜ ፡ ከባድና ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚፈጅ ፡ ሥራ ፡ ነው ። ተከሣሽ ፡ ራሱ ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሥራው ፡ እንዴት ፡ አድካሚ ፡ እንደሚሆን ፡ ለማየት ፡ ይችላል ። ደግሞም ፡ የአንድ ፡ ተከሳሽ ፡ በኋላ ፡ ንጹሕ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ ሥልጣን ፡ ከሚፈቅደው ፡ በላይ ፡ ለመሠራቱ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ አይሆንም ። በተጨማሪም ፡ ተበደልኩ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ጥርጣሬን ፡ በማያስከትል ፡ መንገድ ፤ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ክስ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ አጥጋቢ ፡ ማስረጃ ፡ በማቅረብ ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ጥቅምን ፡ ለማግኘት ፡ ወይም ፡ ለመጉ ዳት ፡ በማሰብ ፡ ክስ ፡ ማቅረቡን ፡ ለማስረዳት ፡ መቻል ፡ አለበት ። እነዚህን ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ (በአጠቃላይ) ፡ ስናይ ፡ ያለው ፡ መፍትሔ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለመዋል ፡ ያለው ፡ ጥቅም ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የመነመነ ፡ እንደሆነ ፡ እንረዳለን ።

በኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕጉ ፡ ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ ድርጊት ፡ ከመጀመሪያው ፡ እንዲወገድ ፡ የማድረጊያ ፡ መፍትሔ ፡ መፈለግ ፡ ነበረ በት ። በኛ ፡ ወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የዓቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ውሳኔ ፡ ለመቃወም ፡ የሚቻለው ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ ላለማቅረብ ፡ በወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ካለ ፡ በቂ ፡ ማስረጃ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ በወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ጭምር ፡ ቢደረግ ፡ ኖሮ ፡ ድርጊቱ ፡ እንዲወገድ ፡ የሚያደርገው ፡ መፍትሔ ፡ ሊሰራ ፡ በቻለ ፡ ነበር ።

ይህ ፡ ዓይነቱ ፡ መፍትሔ ፡ መቼም ፡ የፍርድ ፡ መዘግየትንና ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉን ፡ ሥራውን ፡ እንዳይሠራ ፡ ማስቸገርን ፡ ሊያመጣ ፡ እንደሚችል ፡ ይገባናል ። ነገር ፡ ግን፡ የዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ያደረገውን ፡ ውሳኔ ፡ ለመቃወም ፡ የሚቻለው ፡ ወዲያው ፡ ሳይሆን ፡ ተከሳሹ ፡ መጀመሪያ ፡ በማያጠራጥር ፡ መንገድ ፡ ክስ ፡ የቀረበበት፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ በቻለበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንዲሆን ፡ ቢደረግ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ውጤት ፡ እንዳይደርስ ፡ ያደርገዋል ። በተጨማሪም ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ በዚህ ፡ ደረጃ ፡ ክሱን ፡ በማያጠራጥር ፡ ሁኔታ ፡ እንዲያስረዳ ፡ ሳይደረግ ፡

11. ፍ.ብ.ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፴፪ ፤ ፪፻፴፫ ።

ክሱ ፡ እንዴት ፡ እንደተመሠረተ ፡ ቢያስረዳ ፡ በቂው ፡ ነው ። (ፕሪማ ፡ ፋሺያ) ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ መኖሩን ፡ ከተረዳ ፡ ክሱ ፡ በተለመደው ፡ ሁኔታ፡ እንዲቀጥል ፡ መፍቀድ ፡ አለበት ።

## ፪/ ካለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ መሰናበት ፤ የመፍትሔዎቹ ፡ በቂነት ።

በፊት ፡ እንደተገለጸው ፡ ያሁኑ ፡ ከሳሽ ፡ በወንጀሉ ፡ ክስ ፡ ነፃ ፡ ከተለቀቀ ፡ በኋላ ፡ ለከፍተኛው ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ባቀረበው ፡ አቤቱታ ፡ ከሥራ ፡ ላይ ፡ በተሰናበተ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡ ደሞዝ ፡ (አበል) ፡ እንዲከፍለውና ፡ በቀድሞ ፡ ሥራው ፡ ላይ ፡ እንዲመልሰው ፡ ለመልስ ፡ ሰጭ ፡ (ተከሳሽ) ፡ ትእዛዝ ፡ እንዲሰጥለት ፡ ጠይቆ ፡ ነበር ። ፍርድ ፡ ቤቱም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፭፻፸—፸፩ን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ "ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራው ፡ የተሰናበተ ፡ ሠራተኛ ፡ በኪሣራ ፡ መልክ ፡ የ፮ ፡ ወር ፡ ደሞዙን ፡ የማግኘት ፡ መብት ፡ አለው ። ሥራው ፡ ላይ ፡ እንዲመለስ ፡ የሚያደርገው ፡ ሕጋዊ ፡ መብት ፡ ግን ፡ የለውም" ፡[12] በማለት ፡ ካተተ ፡ በኋላ ፡ ለከሳሽ ፡ የ፩ሺ፭፻፺ ፡ ብር ፡ ኪሣራ ፡ አዞለታል ።

እንዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያስደነግጥ ፡ ቢመስልም ፡ በሕጉ ፡ ከተደነገገው ፡ ጋር ፡ ብዙም ፡ ልዩነት ፡ የለውም ። የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፭፻፸፫ ፡ ለአሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ለማሰናበት ፡ መብት ፡ ይሰጠዋል ። እንደዚህ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ ሠራተኛው ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ኪሣራ ፡ ለማግኘት ፡ መብት ፡ ቢኖረውም ፡ የሚሰጠው ፡ ካሣ ፡ በማንኛውም ፡ ሁኔታ ፡ ቢሆን ፡ በቀን ፡ ሊያ ገኝ ፡ የሚችለው ፡ መካከለኛ ፡ ውጤት ፡ (አቨሬጅ) ፡ በ፩፻፹ ፡ (መቶ ፡ ሰማንያ) ፡ ተባ ዝቶ ፡ ከሚገኘው ፡ ውጤት ፡ ሊበልጥ ፡ አይችልም ።[13]

የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ውል ፡ ልዩ ፡ (የተለየ) ፡ ዓይነት ፡ ውል ፡ ስለሆነ ፡ በጠቅላላ ፡ ግዴታ ፡ (ውል) ፡ ክፍል ፡ ያሉት ፡ መፍትሔዎች ፡ በተለይም ፡ ውልን ፡ በግድ ፡ ለማስ ፈጸም ፡ የሚያዘው ፡ ሕግ ፡ ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራው ፡ ለተሰናበተው ፡ ሠራተኛ ፡ ይረዳዋል ፡ ብሎ ፡ ለመከራከር ፡ ይቻላል ። ውልን ፡ በግዴታ ፡ ለማስፈጸም ፡ ውሉ ፡ ይፈጸምልኝ ፡ ብሎ ፡ ለሚጠይቀው ፡ ተዋዋይ ፡ ወገን ፡ የተለየ ፡ ጥቅም ፡ የሚሰጠው ፡ በሆነ ፡ ጊዜና ፡ አፈጻጸሙ ፡ በባለዕዳው ፡ ነፃነት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ መሰናክል ፡ ሳያደርስ በት ፡ ሊፈጸም ፡ የሚቻል ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ነው ።[14] ሠራተኛውን ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ለመመለስ ፡ የሚሰጥ ፡ ትእዛዝ ፡ ግን ፡ የአሠሪውን ፡ ነፃነት ፡ ሊያሰናክል ፡ ስለሚችል ፡ ክርክሩ ፡ ከመጀመሪያው ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ።[15]

---

12. አሠሪው ፡ ግን ፡ በሠራተኞቹ ፡ መካከል ፡ በአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ሕግ ፡ አ. ፴ ፡ መሠረት ፡ ልዩነት ፡ የፈ ጠረ ፡ እንደሆነ ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ቦርዱ ፡ ከሥራው ፡ ላይ ፡ እንዲመለስ ፡ አዞ ፡ ጠ.ን.ን.ፍ ቤቱም ፡ ውሳኔውን ፡ አጽንቶታል ። ከሳሽ ፡ ተሰራ ፡ ሚካኤል ፡ የሸክላ ፡ ፋብሪካ ፤ ተከሳሽ ፡ የደምቤና ፡ ጓደኞቹ ፡ የሠራተኛ ፡ ማኅበር / ጠ.ን.ን.ፍ ቤት / ፲፱፻፷፬ ፡ ዓ - ም. (አ.ኢ.አ.) ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፤ ቮልዩም ፡ ፫ ፤ ገጽ ፡ ፲፫ ።
13. ስለ ፡ ሠራተኛ ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ ደንብ ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ.ም. አ. ፲ ።
14. ፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፩ሺ፯፻፸፩ ፡
15. አር ፡ ዳቪድ ፡ በአንቀጽ ፡ ፲፪ ፡ ፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ የተደረገ ፡ ገለጻና ፡ ሐተታ ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ ኪንድረድ ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ እንደ ፡ ተረጐመው ፤ ያልታተመ ፤ ቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፡ ሕግ ፡ ፋኩልቲ ፡ መጻሕፍት ፡ ቤት) ፡ ገጽ ፡ ፸፩ ።

እርግጥ ፡ ነው ፡ ሕጉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ዓይነት ፡ መንገድ ፡ ከሥራ ፡ የተሰናበተውን ፡ ሠራተኛ ፡ መብት ፡ ሊጠብቅ ፡ ከቻለ ፡ ወደ ፡ ሥራ ፡ የመመለስ ፡ መብት ፡ ምንም ፡ ዓይነትና ፡ ፍጹምነት ፡ የለውም ። ነገር ፡ ግን ፡ የተሰጠው ፡ መፍትሔ ፡ በጣም ፡ አነስ ተኛ ፡ የሆነ ፡ ካሣ ፡ የሚያስከፍል ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘ ፡ መፍትሔው ፡ የስም ፡ እንጂ ፡ እውነ ተኛ ፡ ሊሆን ፡ ስለማይችል ፡ ነገሩን ፡ አሳዛኝ ፡ ደረጃ ፡ ያደርሰዋል ።

አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ ባሰናበተ ፡ ጊዜ ፡ ካሣ፡ እንዲከፍል ፡ የተደረገበት ፡ ዋናው ፡ ምክንያት ፡ አሠሪው ፡ እንዲህ ፡ ዓይነቱን ፡ ድርጊት ፡ እንዳይፈጽም ፡ ለማገድ ፡ ነው ። እንደ ፡ ሌሎች ፡ በመበልጸግ ፡ ላይ ፡ እንደሚገኙ ፡ አገ ሮች ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ውስጥ ፡ ሠራተኛን ፡ የመቅጠሪያ ፡ ዋጋ ፡ ቀላል ፡ መሆኑ ፡ ለሁሉም ፡ የታወቀ ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ መሠረታዊ፡ የሥራ ፡ ዋጋን ፡ የሚወስን ፡ ሕግ ፡ ባለመኖሩ ፡ ሁኔታው ፡ ሊባባስ ፡ ችሏል ። እውነ ተኛው ፡ ጉዳይ ፡ ይህ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ ከፍተኛው ፡ (መጨረሻው) ፡ ሕጉ ፡ የሚያዘውን ፡ የ፮ ፡ (ስድስት) ፡ ወር ፡ አበል ፡ መክፈል ፡ አሰሪው ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ እንዳያሰናብት ፡ ይገታዋልን? በኛ ፡ አስተሳሰብ ፡ አይገታውም ፡ (አያግደውም) ። በአ ገሪቷ ፡ የሚከፈለው ፡ አበል ፡ አነስተኛነትና ፡ የተሰናበተን ፡ ሰው ፡ ለመተካት ፡ ያለው፡ የሠራተኛ ፡ ብዛት ፡ የመፍትሔውን ፡ ብቁነት ፡ ዋጋ ፡ ቢስ ፡ ያደርገዋል ።

በሌላው ፡ ባልበለጸጉ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ሕግ ፡ መመልከት ፡ የኛን ፡ አሳብ ፡ በተሻለ ፡ መንገድ ፡ ሊገልጸው ፡ ይችላል ። ለምሳሌ ፡ ኢራን ፡ ውስጥ ፡ "ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ ተሰናብቻለሁ ፡ ብሎ ፡ የሚያምን ፡ ሠራተኛ ፡ ለኛ ፡ ተከታታይ ፡ ወሮች ፡ ወይም ፡ በማቋረጥ ፡ ለ፮ ፡ ወር ፡ ለአሠሪው ፡ ሠርቶ ፡ ከሆነ ፡ ያላግባብ ፡ መባረሩን ፡ በተሰናበተ ፡ በ፲፭ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ለኢንዱስት ሪው ፡ ጉባዔ ፡ (ፋክተሪ ፡ ካውንስል) ፡ በማመልከት ፡ ለመቃወም ፡ ይችላል ። ጉዳዩን ፡ በዚህ ፡ ደረጃ ፡ ወይም ፡ ለቦርዱ ፡ አቤቱታ ፡ ካቀረበ ፡ በኋላ ፡ ከረታ ፡ ከተለመደው ፡ ሥራ ፡ ካሣ ፡ በተጨማሪ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ አበል ፡ ድረስ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመ ታዘዝ ፡ ይቻላል ። አሠሪው ፡ ግን ፡ ሠራተኛው ፡ ከሥራ ፡ የተወገደበትን ፡ ቀን ፡ አበል፡ በመክፈል ፡ ወይም ፡ ሥራው ፡ ለመመለስ ፡ ወይም ፡ የተወሰነውን ፡ ኪሣራ ፡ ለመክ ፈል ፡ ይችላል" ።[16]

በሜክሲኮም ፡ "ሠራተኛውን ፡ ሕጋዊ ፡ ባልሆነ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ ያሰናበተ ፡ አሠሪ ፡ ሠራተኛው ፡ በፈለገው ፡ መንገድ ፡ ውሉን ፡ መፈጸም ፡ ወይም ፡ የ፫ ፡ ወር ፡ ደሞዙን ፡ መክፈልና ፡ ሠራተኛው ፡ ከሥራው ፡ ከተሰናበተበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ውሳኔ ፡ እስከሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ሙሉ ፡ አበሉን ፡ መክፈል ፡ አለበት" ።[17]

እንኳን ፡ በውጭ ፡ አገሩና ፡ በኛም ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ደረጃ ፡ እንኳን ፡ መፍ ትሔው ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ። ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራው ፡ የተሰናበ ተው ፡ ሠራተኛ ፡ አነስተኛ ፡ የሆነው ፡ ኪሣራ ፡ የሚከፈለው ፡ አሠሪው ፡ በውል ፡ የገ ባበትን ፡ ግዴታ ፡ ሊፈጽም ፡ አልቻለም ፡ በማለት ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ ዘንድ ፡ ቢያንስ ፡ ቢያንስ ፡ በሌላው ፡ ውል ፡ ጊዜ ፡ እንደሚደረገው ፡ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ውሉ ፡ ባለመፈጸሙ ፡ ያደርሳል ፡ ብሎ ፡ በሚገምተው ፡ መሠረት ፡ ለሠራተኛው ፡

16. ዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ክፍል ፡ የሌበር ፡ ሎው ፡ እንድ ፡ ፕራክቲስ ፡ ኢን. ኢራን ፡ (፲፱፻፷፱ ፡ እ.ኤ.አ) ፡ ገጽ ፡ ፮፱ ፡ (እንግሊዝኛ) ።
17. ዩ.ኤ.ስ. ዲፓርትመንት ፡ ኦፍ ፡ ሌበር ፡ ሎው ፡ አንድ ፡ ፕራክቲስ ፡ ኢን. ሜክሲኮ ፡ (፲፱፻፷፫ ፡ እ.ኤ.አ.) ፡ ገጽ ፡ ፷፩ ፡ (እንግሊዝኛ) ።

ከሥራ ፡ አይከፈለውምን ?[18] መቼም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከእውነት ፡ የራቀ ፡ ሀሳብ ፡ በማ ቅረብ ፡ አእምሮ ፡ ባለው ፡ ሰው ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ ከሥራው ፡ የተሰናበተ ፡ ሠራተኛ ፡ ተመጣጣኝ ፡ ሥራ ፡ ለማግኘት ፡ የሚፈጅበት ፡ ጊዜ ፡ ፩፻፹ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ካላለ ፡ በተቀር ፡ መፍትሔው ፡ በዚህም ፡ ደረጃ ፡ እንኳን ፡ ውድቅ ፡ ይሆናል ።

የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ሕጎቻችን ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ የኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ እንዲፋ ጠን ፡ በማሰብ ፡ በአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ ጥሩ ፡ መንገድ ፡ እንዲይዝ ፡ ነው ። ስለዚህም ፡ የሁለቱ ፡ ወገኖች ፡ የጥቅም ፡ ፍላጎት ፡ ሳይነካ ፡ ትክክ ለኛ ፡ የሆነ ፡ ግንኙነት ፡ እንዲፈጠር ፡ መደረግ ፡ አለበት ። የአሁኑ ፡ ጉዳይ ፡ ግን ፡ በግልጽ ፡ እንደሚያሳየው ፡ ሠራተኛውን ፡ በመጉዳት ፡ ጥቅሙ ፡ ወደ ፡ አሰሪው ፡ ያመዘነ ፡ ይመስላል ። ይህን ፡ ዓይነት ፡ ያልተስተካከለ ፡ መፍትሔ ፡ ለማቃናት ፡ ሕግ ፡ አውጪው ፡ ክፍል ፡ በማንኛውም ፡ ጊዜ ፡ አንድን ፡ ሰው ፡ ከሥራ ፡ ለማሰናበት ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ፡ ብሎ ፡ መደንገግ ፡ አለበት ። ይህም ፡ መፍ ትሔ ፡ እኛም ፡ የአለም ፡ ሠራተኞች ፡ ድርጅትም ፡[19] ጥሩ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ካቀረበው ፡ ሀሳብ ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ ነው ። ይህም ፡ ባይሆን ፡ እንደ ፡ የሁለቱን ፡ ወገኖች ፡ የኅብ ረት ፡ ክርክር ፡ ኃይል ፡ መጠን ፤ በአገሪቷ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ብልጽግና፤ የሥራ ፡ ፊት ፡ ኢንሹራንስ ፡ ወይም ፡ ጥቅም ፡ ያሉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ በመመልከት ፡ በዛ ፡ ያለ ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባውን ፡ ከፍተኛውን ፡ የኪሣራ ፡ መጠን ፡ መደንገግ ፡ ነው ።

የሚከተለውን ፡ ማስታወስ ፡ ግን ፡ ጠቃሚ ፡ ይሆናል ። የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ሕግና ፡[20] ስለ ፡ ሠራተኛ ፡ መሠረታዊ ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ የወጣው ፡ ደንብ ፡[21] ሕጎቹ ፡ ከመውጣታቸው ፡ በፊት ፡ ወይም ፡ በኋላ ፡ በግል ፡ የተደረገ ፡ የሥራ ፡ ውል ፤ በሠራተ ኞች ፡ የአስተዳደር ፡ ደንብ ፡ በተመዘገበ ፡ የኅብረት ፡ ስምምነት ፡ ወይም ፡ ብይን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አኳኋን ፡ ሠራተኞች ፡ የሚያገኙት ፡ ማናቸውም ፡ የተሻለ ፡ ጥቅም ፡ ከሕጉ ፡ በላይ ፡ እንደሚጸና ፡ ደንግገዋል ። ሕጉ ፡ እውነተኛውንና ፡ ትክክለኛውን ፡ መሥመር ፡ እስኪይዝ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ አለመስተካከል ፡ ይህ ፡ ሊቀንሰው ፡ ይችላል ። እንዲያውም ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ ግቦች ፡ ለማሟላት ፡ በዚሀ ፡ ጥበብ ፡ የሚጠ ቀሙ ፡ ብዙ ፡ በቅርቡ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የዋሉ ፡ የኅብረት ፡ ስምምነቶችን ፡ እናገኛለን ። ለምሳሌ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የነዳጅ ፡ ዘይት ፡ ማጣሪያ ፡ ሠራተኞች ፡ መካከል ፡ የተፈረመው ፡ የኅብረት ፡ ስምምነት ፡ ላይ ፡ የሚከተለውን ፡ እናገኛለን ፤ "አንድ ፡ ሠራተኛ ፡ ካለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራው ፡ ሊሰናበት ፤ ሊወገድ ፡ ወይም ፡ ሊዛወር ፡ አይችልም ።"[22] እንዲሁም ፡ ካለ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ በሚሰናበትበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከፈለው ፡ ካሣ ፡ ሕጉ ፡ ከሚያዘው ፡ በላይ ፡ እንዲሆን ፡ በኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ (እ ፡ ማ)ና ፡

18. ፍ/ብሔር ፡ ሕግ ፡ አንቀጽ ፡ ፪ሺ፭፻፶፱ ።

19. አንቀጽ ፡ ፪/ ፩) የዓለም ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ አሠሪው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ከሥራ ፡ ማሰናበት ፡ የተሰጠ ፡ አሳብ ፡ (ቁጥር ፡ ፩፻፶፰ ፡ ሰኔ ፡ ፳፪ ፡ ፲፱፻፹፪ ፡ እ.ኤ.አ.) ፡ የሚከተለውን ፡ ይላል ፡ "ብቁ ፡ የሆነ ፡ ምክንያት ፡ ከሠራተኛው ፡ የሥራ ፡ ችሎታ ፡ ወይም ፡ የሠራተኛውን ፡ ጠባይ ፡ የሚመለከት ፡ ሲሆን ፡ ወይም ፡ ራሱ ፡ የአሠሪው ፡ የሥራ ፡ ቦታ ፡ በሚፈቅደው ፡ የሥራ ፡ አሠራር ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ካልሆነ ፡ አሠሪ ፡ የሠራተኛውን ፡ ሥራ ፡ ሊያቋርጥ ፡ አይችልም" ።

20. የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ሕግ ፡ ፲፱፻፹፭ በቁጥር ፡ ፵፪ ፡ እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አን. ፴፰

21. የሠራተኛ ፡ መሠረታዊው ፡ የሥራ ፡ ሁኔታ ፡ ደንብ ፡ ፲፱፻፹፮ ፡ ዓ ፡ ም ፤ እላይ ፡ በቁጥር ፡ ፲፱ ፡ የተጠቀ ሰው ፤ አንቀጽ ፡ ፯ ።

22. በኢትዮጵያ ፡ የዘይት ፡ ማጣሪያ ፡ (እ.ማ)ና ፡ በኢትዮጵያ ፡ የዘይት ፡ ማጣሪያ ፡ ፋብሪካ ፡ ሠራተኞች ፡ መካከል ፡ በጥር ፡ ፩ ፡ ፲፱፻፸፩ ፡ ዓ. ም. (እ.ኤ.አ.) የተፈረመው ፡ የሕብረት ፡ ስምምነት ፡ አንቀጽ ፡ ፳ ፡ (ሀ) ።

በኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ ሠራተኞች ፡ ማኅበር ፡ መካከል ፡ የተፈረመው ፡ የሕብረት ፡ ስምምነት ፡ ይደነግጋል ።[23]

## መደምደሚያ ፡

በአቀረብነው ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ መሠረት ፡ ክሱ ፡ ከፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ጉዳዩ ፡ ስለሚጣራበት ፡ መንገድና ፡ በኛ ፡ አሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ሕጐች ፡ መሠረት ፡ የሥራው ፡ ውል ፡ ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ በሚቋረጥበት ፡ ጊዜ ፡ ሊፈጠር ፡ የሚችለውን ፡ ሁኔታ ፡ ለማቅረብ ፡ ሞክረናል ። ክሱ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ከመቅረቡ ፡ በፊት ፡ ጉዳዩ ፡ ስለሚጣራበት ፡ ሁኔታ ፡ ያሉት ፡ መፍትሔዎች ፡ የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕጉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ መርዳታቸውን ፡ አግኝተናል ። ነገር ፡ ግን ፡ በተመጣጣኝ ፡ ማስረጃ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ ይኸውም ፡ ንጹሕ ፡ ሰዎች ፡ ሳይነኩ ፡ መቃለፍ ፡ አለባቸው ፡ በሚለው ፡ ግብ ፡ ግን ፡ መፍትሔው ፡ በቂ ፡ ሆኖ ፡ አላገኘነውም ። ለዚህ ፡ ዓይነቱም ፡ ጉዳይ ፡ መድኀን ፡ ይሆናል ፡ ብለን ፡ አሳብ ፡ አቅርበናል ። ይኸውም ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ክስ ፡ ሳለማቅረብ ፡ በወሰነበት ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔውን ፡ ለመቃወም ፡ የተሰጠው ፡ መብት ፡ ዓቃቤ ፡ ሕጉ ፡ ያላግባብ ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ በወሰነበትም ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያስፈልጋል ፡ የሚል ፡ ነው ።

ስለሠራተኛ ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ከሥራ ፡ በሚሰናበትም ፡ ጊዜ ፡ አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ ወጪ ፡ ሊሽኝ ፡ በመቻሉ ፡ የአሠሪና ፡ ሠራተኛ ፡ ሕጐቻችን ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሚያመዝኑ ፡ ሆነው ፡ አግኝተናቸዋል ። ያለውን ፡ ሕጋዊ ፡ ፍትሕ ፡ የተስተካከለ ፡ (ሚዛናዊ) ፡ ለማድረግ ፡ መጀመሪያ ፡ ያለ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ሠራተኛ ፡ ከሥራው ፡ እንዳይሰናበት ፡ እንዲደረግ ፡ አሳብ ፡ አቅርበናል ። ይህ ፡ ካል ሆነ ፡ ግን ፡ የሕጉ ፡ ዓላማ ፡ አሠሪው ፡ ሠራተኛውን ፡ ያለበቂ ፡ ምክንያት ፡ እንዳያሰናብትና ፡ የሠራተኛውን ፡ ይዞታ ፡ የጠበቀ ፡ ለማድረግ ፡ ከሆነ ፡ በሕጉ ፡ ከተደነገገው ፡ የ፲ ፡ ወር ፡ ካሣ ፡ ክፍያ ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ ከፍተኛና ፡ ጠበቅ ፡ ያለ ፡ መፍትሔ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያስፈልጋል ። የገንዘቡን ፡ መጠን ፡ ወስኖ ፡ ለማቅረብ ፡ በአገሪቷ ፡ ያለውን ፡ የአሠሪና ሠራተኛ ፡ ሁኔታ ፡ በጥንቃቄ ፡ ማጥናት ፡ ስለሚያስፈልግና ፡ ጥናቱም ፡ ሰፊና ፡ ከባድ ፡ ስለሚሆን ፡ በዚች ፡ ባጭር ፡ የፍርድ ፡ ጉዳይ ፡ (ሁተታ) ፡ አሳብ ፡ ውስጥ ፡ ለማቅረብ ፡ ስለማይቻል ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ ገንዘብ ፡ ይከፈል ፡ ብለን ፡ አሳብ ፡ ከማቅረብ ፡ ተቆጥበናል ።

---

3 . በኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድና ፡ (ኢ.ማ.) በኢ/አየር ፡ መንገድ ፡ ሠራተኞች ፡ አንድነት ፡ ማኅበር ፡ መካከል ፡ በጥር ፡ ፩/፲፱፻፸፭ ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ የተፈረመው ፡ የኅብረት ፡ ስምምነት ፤ አንቀጽ ፡ ፲ ፡ (ሠ)።